# በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ ላይ የተደረገ የሙስና ስጋት ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዚያ /2015ዓም

አዲስ አበባ

**ማውጫ**


| ርእስ | ገጽ |
|---|---|
| **የጥናቱ ማጠቃለያ ( Executive Summary )** | **2** |
| ***ክፍል 1፡ መግቢያ*** | ***4*** |
| 1.1. የጥናቱ ዳራ | 5 |
| 1.2. የዘርፉ አጠቃላይ መረጀ | 8 |
| 1.2.1 ዘርፉ የተቋቋመበት አላማና ተግባራት | 8 |
| 1.2.2 በዘርፉ ያሉና በጥናቱ የተካተቱ የፌደራል ተቋማት | 11 |
| 1.3. የጥናቱ አላማ | 11 |
| ***ክፍል 2፡ የዘርፉ የሙስና ስጋት ጥናት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ*** | ***12*** |
| - *አጠቃላይ መረጃ* | *12* |
| - መሬት አስተዳደርና ሙስና | 13 |
| - የመሬት አስተዳደርና ሙስና በኢትዮጵያ | 14 |
| - የግንባታ ሙስና | 15 |
| ***ክፍል 3፡ የጥናቱ መረጃ ሂደትና የትንተና ዘዴ*** | ***17*** |
| 3.1. የጥናቱ ቦታ | 17 |
| 3.2. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች | 17 |
| 3.3. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ | 18 |
| 3.4. የጥናቱ ተግዳሮቶች | 18 |
| ***ክፍል 4፡ ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት ትንተና*** | ***20*** |
| 4.1. የተቋሙ አደረጃጀት | 20 |
| 4.2. ተጠያቂነት ማስፈን | 2022 |
| 4.3. የተቋማት ግልፅነት | 21 |
| 4.4. አዋጅ ደንብና መመሪያ | 22 |
| 4.5. የተቋማት ንብረት አስተዳደር | 25 |
| 4.6. የግዥ አስተዳደር | 25 |
| 4.7. የሰው ሃበት አስተዳደር | 26 |
| 4.8. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ | 27 |
| 4.9. የፕሮጀክቶች አስተዳደር | 28 |
| 4.10. ኦዲትና ቁጥጥር | 29 |
| 4.11. የሙሰና ስጋት ---------------------------------------------------------29 | |
| ***ክፍል 5፡ የመፍትሔ ሃሳቦች (ምክረ-ሃሳብ)----------------------------------30*** | |

# የጥናቱ ማጠቃለያ (Executive Summary)

ሙስና በአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ በማስከተል የተቋማትን የስራ አፈጻጸም ይጎዳል፣ ሀብት ያባክናል ተቋማትንም የማፍረስ አደጋ ሊያስከትል የሚችል አደገኛ የሆነ የወንጀል አይነት ነው፡፡ ኢትዮጵያም በዚህ ወንጀል ከተጎዱ ሀገራት አንዷ በመሆኗ የፌዴራል የስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይህንን ብልሹ አሰራር ጥናትን መሰረት ባደረገ መልኩ መከላከል የመሪነት ሚና ተሰጥቶት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ጥናትም የዚህ ጥረት አንዱ መገለጫ ነው፡፡

ለጥናቱ ክንውን የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ቼክ-ሊስት (የዳሰሳ መጠይቅ) እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ሲሆኑ ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

የጥናት ቡድን አባላት የተቋማት የተለያዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በማወያየት እንዲሁም (እንዳስፈላጊነቱ) በምልከታ የተዘጋጀውን ቼክ-ሊስት እንዲሞለ ተደርጓል፡፡ ይህን ጥናት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በቼክ-ሊስት ላይ የተነሱ ነጥቦች አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጣቸው በሰነድ ወይም በምልከታ ሲረጋገጡ ብቻ መሆኑ ነው፡፡

የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከል ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ተዳሰዋል፡፡

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ነው፡፡ ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) አሀዛዊ መረጃዎችን በመተንተን ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች (ቼክ-ሊስት፣ ሰነዶች እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን በመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ተጠቅሟል፡፡

ጥናቱ የተዘረዘሩትን ዘዴዎች በመጠቀም ጥናቱ ባካተታቸው አስራአንድ ርእሰ-ጉዳዮቸ ማለትም (የተቋሙ አደረጃጀት፣ ተጠያቂነት ማስፈን፣ የተቋማት ግልፅነት፣ አዋጅ ደንብና መመሪያ፣

የተቋማት ንብረት አስተዳደር፣ የግዥ አስተዳደር፣ የሰው ሃበት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር፣ ኦዲትና ቁጥጥር፣ የሙሰና ስጋት) የዘረፋና በስሩ ያሉ ተቋማት ነባራዊ ሁኔታ ለመረዳት ሞክራል፡፡ ከዚህ መረጃ በመነሳትም ያሉ የሙሰና ስጋቶችን በመለየት መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ሃሳቦችን አቅርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በአስሩ ርእሰ-ጉዳዮች የሚከተሉት ችግሮች ተለይተዋል፡፡ እነሱም በተወሰኑ ተቋማት ተቋማዊ የህግ ባለሙያ አለመኖር፣ የተደራጀ መደበኛ ቅንጅታዊ አሰራ ስርዓት አለመዘርጋቱን፣ ድርጅቶች የስነምግባር ደንባቸውን ወቅታዊና፣ ዘመናዊ የንብረት አስተዳደር ስርዓት (የካይዘን ስርዓትን) ትግበራ በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ተግባራዊ ያልተደረገ፣ በግዥ እቅድ አለመመራት፣ የገበያ ጥናት ሳያካሄዱ ግዥ መፈጸም እና ሁሉም የዘርፉ ተቋምት ዘመናዊ የግዥ ስርዓት(EGP) አለመጠቀማቸውን፣ ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ የማጣራት፣ ፕሮጀክቶች መካከል የተወሰኑት በተያዘላቸው ጊዜ አለመጠናቀቅ፣ በፕሮጀክቶች የዋጋ ለዩነት መታየትና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች ተደራሽ አለመደረግ ናቸው፡፡ ለነዚህ ችግሮች ጥናቱ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ሃሳቦችን አቅርባል፡፡ በጥናቱ የተካተቱ እነኚህን ሃሳቦች ቢተገበሩ በየርእሰ-ጉዳዩ ክፍተቶችን በማስወገድ ያሉ የሙስና ስጋቶችን ሊቀንሱ እንደሚችሉ ይታምናል፡፡

# ክፍል አንድ፡ መግቢያ

የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስና በሃገሪቱ ባሉ ተቋማት የከፋ ደረጃ ላይ መድረስን በመረዳት ችግሩን በዘላቂነት መፍታት ይቻል ዘንድ የስራ አፈጻጸምና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት እያካሄደ ይገኛል፡፡ ጥናቱ በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ ያለውን የሙስና ስጋት የሚመለከት ነው፡፡ ሀገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ መንግስት የሚያልመውን የብልጽግና ጉዞ ማሰሳካት እንዲቻል በሀገሪቱ ያሉ የግልና መንግስታዊ ተቋማት የተሰጣቸውን ሀገራዊ ሃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን ለማሳካት ደግሞ ከሙስና ጋር የተያያዘ ጉዳዮችን መዳሰስ፣ መለየትና አስፈላጊውን የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡ በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍም አንዱ ነው፡፡ ሙስና በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ በማስከተል ሃገር እንደሃገር በማይቀጥልበት ደረጃ የማድረስ ወይም ተቋማትን የማፍረስ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ተለዋዋጭነት ባህሪ ያለው አደገኛ የሆነ የወንጀል አይነት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሃገራት ይህን የተለዋዋጭነት ባህሪ እያሳየ ያለውን የወንጀል ዓይነት ሊመጥን የሚችል የመከላከያ ስልት በመንደፍ ስራ ላይ ለማዋል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ጥናትም የተጠቀሰውን ችግር መሰረት በማድረግ የተሰራ ነው፡፡ ጥናቱ በአምስት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን፤ በክፍል አንድ የጥናቱ ዳራ (background)፣ አላማዎች፣ የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ የጥናቱ ስነዘዴና የጥናቱ ተግዳሮቶችን አካቷል፡፡ በክፍል ሁለት የዘርፉ የሙስና ስጋት ጥናት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ ሲሆን ክፍል ሶስት የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደትና የትንተና ዘዴ ይዟል፡፡ ክፍል አራት ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት ትንተና ተካሂዶበታል፡፡ በክፍል አምስት ለተለዩ የሙስና ስጋቶች የመፍትሀ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ሙስና የአንድን አገር መልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ እድገት እና የሰብአዊ መብት መከበር በከፍተኛ ሁኔታ ከሚጎዱ ችግሮች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ሙስና ማለት ባለስልጣኖች/ሀላፊዎች ከህብረተሰቡ የተሰጣቸውን አደራ ለግል መበልጸጊያ የማዋል ብልሹ አሰራር ማለት ነው፡፡

ሐቀኝነትን የማጉደል ወይም ሕገወጥ ባህሪ ማለት ነው፡፡ ሙስና የህግ የበላይነትን በማጣመም እና ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆነውን ተቋማዊ መሰረት በማቀጨጭ ልማትን ያዳክማል፣ ለማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ማነቆ ይሆናል፣ በመሰረተ ልማት፣ በተቋማት እና በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስትመንቶችን በማዳከም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምህዳርን ያጎለብታል፡፡ የሞራል እሴቶች ማሽቆልቆል እና ህገ-መንግስታዊ ተቋማትን እና ስልጣንን አለማክበር የሙስና መገለጫዎች ናቸዉ፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል፤ አገሮች፣ ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል፡፡ እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና/ወይም የግሉ ሴክተር ድርጅቶች ጥረታቸውን እና ሀብታቸውን በጣም አንገብጋቢ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል፡፡

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት ህጎችን በማውጣት እና በመተግበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናትና ምርምር በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው፡፡ በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ግን ለሙስና ስጋት የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ አደረጃጀቶችና አሰራሮችን በመለየት ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት

ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ ባለመሰራቱ፣ ሙስና በየጊዜው እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ሥራን በተቋም ደረጃ የሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አደራጅቶ ወደ ተግባር ቢገባም፣ እስካሁን በተቋማቱ ውስጥ የሙስና መከላከል ተግባራት የተገኘዉ ዉጤት በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ደርሶ አልተገኘም፡፡

በተለያዩ ዘርፎች ስር በሚገኙ ተቋማት ሊከሰቱ ለሚችሉት የሙስና ዓይነቶች ፣ የህጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ ተቋማዊ ባህል፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራረብ፣ አያያዝ እና አፈታት የመረጃ አያያዝ ደካማነት፣…ወዘተ እንደ ተቋማዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት ክስተቶች በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴ ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡በመሆኑም ይህን የሙስና ሥጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ ሲባል በከተማና መሠረተ ልማት ዘርፍ ስር ባሉ ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ የሆነ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ግመገማዊ ጥናት በማካሄድና በተቋማት የጎላ ተሳትፎ የሙስና መከላከያ ምክረ ሀሳቦችን ለማቅረብ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

## 1.2. የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ

### 1.2.1. ዘርፉ የተቋቋመበት አላማ እና የሚያከናዉናቸው ተግባራት

**መንግስታት በሃገራቸው የሚያቋቁሟቸውን** ተቋማት ሲደራጁ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት በሚያስችል መልኩ ግልጽ ዓላማ ያላቸው፣ ከሌሎች ተቋማት ሥልጣንና ተግባር ጋር የማይጋጭና ተናባቢ የሆነ ተግባርና ኃላፊነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትም በሀገሪቱ ያሉ ተቋማት በቅንጅት የሚሰሩ፣ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ የሆነ፣ ብክነትን የሚቀንስና ውጤታማነትን የሚያበረታታና፣ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ፣ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ደንግጓል።

በዚህ ድንጋጌ መሰረት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ተቀምጧል።

ሀ. የከተማና ኮንስትራክሽንና መሠረተ ልማትን ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ እና መሠረተ ልማት በውጤታማነትና በቅንጅት መከናወኑን የሚያረጋግጡ፣ የከተማ መሬትን እና ከመሬት ጋር የተያያዘ ሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመመዝገብ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሀገራዊ የተቀናጀ የመሠረተ ልማት፣ መዋቅራዊ እና ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ. ሀገራዊ የመንገድ መሠረተ ልማት ሥራዎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታነትንና ፍትሐዊ ተደራሽነትን መሠረት ባደረገ መልኩ መከናወናቸውን ይከታተላል፤

መ. በሀገር አቀፍ ደረጃ የከተሞች መዋቅራዊና መሠረታዊ ማስተር ፕላን ዝግጅትን ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ሠ. ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ የመሬት ይዞታ እና የንብረት ካሳ ቀመርና የነጠላ ዋጋ ያዘጋጃል፤

ረ. ከገጠር ወደ ከተማ የሚሸጋገሩ አካባቢዎችን በተመለከተ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን፣ የልማት ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ስታንዳርዶችን ያወጣል፣ ይቆጣጠራል፤

ሰ) አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የተቀናጀ የአከታተም ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ከተሞች ከሀገር አቀፍና ከክልል አቀፍ የልማት ዕቅዶችና ከተቀናጀ የከተሞች ማስተር ፕላን ጋር ተጣጥመው የሚመሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሸ. ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናቶችን ያደርጋል፣ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ያመነጫል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤ ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

ቀ) የተመጣጠነ የከተሞች እድገትና የሕዝብ አሰፋፈር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፤ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት ጋር በመቀናጀት ይተገብራል፤

በ) የከተሞችን መሬት በቁጠባ እና በውጤታማነት መጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ የአሠራር ስልት ይነድፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ተ) የከተሞችን ፈርጅ እና ሚና መወሰኛ መመዘኛ ያወጣል፤ የከተሞችን ጽዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስታንዳርድ ያወጣል፤ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ቸ) ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ እና መልካም አስተዳደር እንዲያሰፍኑ ለክልሎች የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፤

ኀ) የአዲስ አበባና የድሬዳዋ የከተማ አስተዳደሮችን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን እና መሠረተ ልማት ሥራ እንቅስቃሴዎችን ይደግፋል፣ይከታተላል፤

ነ) የነፃ ገበያ ሥርዓት ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን የካዳስተር እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይት ሥርዓት እንዲገነባ ያደርጋል፤ በከተሞች ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የለማ መሬት አቅርቦት ለማረጋገጥ ድጋፍ ይሠጣል፤

ኘ) የከተሞች ልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ሥርዓት ያጠናል፣ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ፈንድ ያሰባስባል፣ ለአፈጻጸሙም ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ኣ) ለዜጎች የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ለማሟላት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ በሚመለከታቸው አካላት ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይደግፋል፤ በቤቶች ልማት ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

ከ) በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤ ሀገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ በዲዛይን፣ በጨረታና፣ በኮንትራት ይዘት ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ኸ) በማንኛውም ዘርፍ የሚደረጉ የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ግዢዎች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር መደረጉን ይከታተላል፤ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ደረጃ መውጣቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፤

ወ) በፌደራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ የሕንፃ ኮድና ስታንዳርዶች በከተሞች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ኃይል አቅም እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፤

ዘ) በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ያካሂዳል፤ የሀገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ግብዓት መጠቀምን ያበረታታል፤

ዠ) የከተማ መሬትና ከመሬት ጋር የተያያዘ ሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ መለያ ኮዶች ሥርዓት ያወጣል እንዲሁም የመለያ ኮዶቹ በሀገር አቀፍ ደረጃ በከተሞች ተጣጥመው ተፈጻሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

የ) የካዳስተር ባለሙያዎች ሥልጠና ፕሮግራም ስለሚስፋፋበትና የሙያ ብቃት የሚረጋገጥበት ሥርዓት ስለሚጠና ከርበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

ደ) የከተማ መሬትና ከመሬት ጋር የተያያዘ ሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባን ሚያከናውኑ ተቋማት እንዲያደራጁ ለክልል ከተሞች ድጋፍ ያደርጋል፣ ተቋማቱ ደረጃውን የጠበቀ ምዝገባ ማከናወን እንዲችሉ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤

ጀ) የከተማ የምግብ ዋስትና ሥራን ያስተባብራል፤

ገ) ከተሞች ከሀገር አቀፍና ከክልል አቀፍ የልማት ዕቅዶችና ከተቀናጀ የከተሞች ፕላን ጋር ተጣጥመው የሚመሩበትን አቅጣጫ ይነድፋል፤

ጠ) የሪል ስቴት ልማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ ሲጸደቅም ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤

## *1.2.2. በዘርፉ ስር ያሉ እና በጥናቱ የተካተቱ የፌዴራል ተቋማት*

የከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ "የመሰረተ ልማት ተደራሽነትን በማረጋገጥ ምቹና የፋይናንስ አቅማቸው የጎለበተ ከተሞችንና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ሴክተር ለመፍጠርና የተዘረዘሩትን ተያያዥ ተግባርና ሀላፊነቶች ለመወጣት ያስችለው ዘንድ " በስሩ አራት የተለያዩ ተቋማትን በማደራጀት እየሰራ ይገኛል፡፡ እነኚህም ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እና የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ሲሆኑ ሁሉም በጥናቱ ተካተዋል፡፡

## *1.3. የጥናቱ አላማ*

### 1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ፡-

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በከተማ እና መሰረተ ልማት ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሰራር ስርዓት በመገምገም የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡

### 1.3.2. ዝርዝር አላማዎች፡-

- በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሠራር ስርዓትን መገምገም፤
- የሙስና ተጋላጭነትን ደረጃን መለየትና መተንተን፤
- ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ስልቶችን ለማመላከት ነው

# ክፍል 2፡ የዘርፉ የሙስና ስጋት ጥናት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

*አጠቃላይ መረጃ*

በዚህ ክፍል በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍና በስሩ ባሉ ተቋማት አገልግሎቶች ላይ የሚከናወን ሙሰናና የሚታዩ የሙስና ስጋቶች ምን አይነት ገጽታ እንዳለው የአለም አቀፍ ተሞክሮና በሃገራችንም እውነታ ለመዳሰስ ተሞክራል፡፡

በከተሞች የሚኖረው የአለም ህዝብ መጠን በ1950 ከነበረበት 751 ሚሊዮን በ2018 ወደ 4.2 ቢሊዮን በፍጥነት አድጓል። እንደ የተባበሩት መንግስታት (ተመድ) የአለም የከተሞች እድገት ክለሳ ዛሬ 55% የሚሆነው የአለም ህዝብ በከተማ ውስጥ ይኖራል፡፡ በ2050 ይህ ድርሻ ወደ 70% አካባቢ ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል። ዓለም ወደ ከተሜነት በቀጠለችበት ወቅት፣ ብዙ አገሮች እያደገ የሚሄደውን የከተማ ህዝባቸውን ፍላጎት ለማሟላት፣ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ውስጥ ፈተናዎች ይገጥሟቸዋል።

እ.ኤ.አ. በ 2030 የተባበሩት መንግስታት ዘላቂ ልማት ግብ 11 (ኤስዲጂ 11) በቂ ፣ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤቶችን በማቅረብ ከተሞችን እና የሰው ሰፈራዎችን አካታች ፣ደህንነቱ የተጠበቀ ፣የሚቋቋሙት እና ዘላቂ እንዲሆኑ ለማድረግ ያለመ ነው።

የህዝብ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከተሞች ዘላቂነት ያላቸው እና በቂ የህዝብ አገልግሎቶችን እንደ የህዝብ ትራንስፖርት፣ የቆሻሻ አወጋገድ እና ኢነርጂ እንዲሁም ለህዝብ መሠረተ ልማት፣ ተደራሽ የሕዝብ ተቋማት እንደ ትምህርት ቤቶች እና ሆስፒታሎች እንዲሁም ለመዝናኛ አገልግሎት መስጠት አለባቸው። እንደ ፓርኮች፣ የስፖርት ሜዳዎች እና ኩሬዎች:: ከሚሰጡ አገልግሎቶች የመሬት አስተዳደርና የግንባታው ዘርፍ ያለው ሙስና ከመጠን በላይ የከፋ በመሆኑ በነ፝ኚእ አሰራሮች ያለውን አገርአቀፋዊና አለምአቀፋዊ ሁኔታ እንደሚከተለው ይቀርባሉ

## የከተማ መሬት አስተዳደርና ሙስና

መሬት ለዕድገትና ለልማት ቁልፍ ግብአት ነው። የገጠር መሬት ማግኘት ድህነትን ለመቀነስ እና ዘላቂ ልማትን ለማጎልበት ወሳኝ ነው። የተካሄደው ሰፊ ጥናትና ምርምር ውስን ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ በመሬት ዘርፍ ያለው ሙስና ከፍተኛ ችግር መሆኑን ይጠቁማሉ።

በመሬት አስተዳደር ውስጥ ያለው ሙስና ከፍተኛ የህብረተሰብ ወጪ አለው፣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰዎች አኗኗር ላይ ትልቅ ተጽእኖ ይኖረዋል። በዚህ ዘርፍ ያለው ሙስና የዜጎችን የመሬት ተጠቃሚነት ይቀንሳል፣ የዜጎችን ኑሮ ይጎዳል። ሴቶች፣ ወጣቶች እና አናሳ ብሄረሰቦች መሬት የማግኘት መብታቸው በሙስና በመታገዱ ለከፋ ችግር ይጋለጣሉ።

በብዙ ቦታዎች  በዕለት ተዕለት የመሬት አስተዳደር አገልግሎቶች ሙስና የተለመደ ተግባር ነው። ለምሳሌ፡ መሬት አገልግሎቶች አካላዊ እቅድ ማውጣት፣ ካርታ ስራ፣ ዳኝነት፣ ዳሰሳ ጥናት፣ ግምገማ፣ ግብር አወሳሰን እና ምዝገባን ያካትታሉ። እያንዳንዳቸው እነዚህ አገልግሎቶች እንደ መሬት ፍለጋ፣ የመሬት ማስተላለፎች፣ ወዘተ ባሉ በርካታ ንዑስ አገልግሎቶች ሊከፋፈሉ ይችላሉ።

በአጠቃላይ የመሬት አስተዳደር ጥራት ያለው የመሬት አገልግሎት አሰጣጥን ለማረጋገጥ ተጠያቂ፣ ምላሽ ሰጪ፣ ህዝብን ያማከለ እና ግልጽ መሆን እንዳለበት በፅንሰ-ሀሳብ ደረጃ ይቀርባል።

ይሁን እንጂ ይህ በብዙ የዓለም ክፍሎች ካለው እውነታ የራቀ ነው። ለምሳሌ፡ በታንዛኒያ፣ በኬንያ እና በኡጋንዳ የመሬት አገልግሎት ለጉቦ ተጋላጭ ከሆኑ ዘርፎች በሶስተኛው ደረጃ ያለ ዘርፍ ነው። በሜክሲኮ የመሬት አገልግሎት ከፍተኛ የጉቦ ደረጃ ካላቸው የአስተዳደር ዘርፎች መካከል አንዱ ሲሆን በባንግላዲሽ የመሬት አገልግሎት በጣም የከፋ የጉቦ መጠን እና ከፍተኛ የጉቦ ወጭ ካላቸው ሶስት ተቋማት መካከል አንዱ ነው።

በመሬት አስተዳደር ውስጥ ከሚታዩ ሙስናዎች መካከል ጉቦ፣ ጾታዊ ምዝበራ፣ ማጭበርበር እና ድጋፍ መስጠትን ያካትታሉ።

ሴቶች በጉቦ ምትክ ለፆታዊ ጥቅማጥቅሞች ሊጋለጡ ይችላሉ። ማጭበርበር ከመሬት ጋር የተያያዙ ሰነዶችን እንደመጭበርበር፣ በቀያሾች እና በመሬት አስተዳዳሪዎች የሐሰት መለኪያዎች ወይም የመሬት ባለይዞታዎች የንብረት ማርከሮች ሊሆኑ ይችላሉ።

መሬት በኤሊቶች የፖለቲካ ድጋፍን ለማግኘት ወይም የደንበኛ እና የደንበኛ ግንኙነትን ለማስቀጠል ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

የመሬት አስተዳደርን የሚመለከቱ ሕጎች ውስብስብ እና ግልጽ ያልሆኑ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይህም በሙስና የተዘፈቁ ባለስልጣናት የራሳቸውን ጥቅም በሚያስቡ ባለስልጣናት የመጎሳቆል እድሎችን ይጨምራሉ፡፡

ከፍተኛ ሙስናና የመልካም አስተዳደር ችግር የመሬት ባለሀብቶችን የሚስቡ አገሮች መለያ ናቸው፡፡ እ.ኤ.አ. ከ2000 እስከ 2011 ባለው ጊዜ ውስጥ የመሬት ስምምነቶች ከተስማሙባቸው 56 አገሮች ውስጥ ከሶስት አራተኛ በላይ የሚሆኑት እንደ ድምፅ እና ተጠያቂነት፣ የቁጥጥር ጥራት፣ የሕግ የበላይነት እና የሙስና ቁጥጥር በመሳሰሉት የአስተዳደር አመልካቾች ከአማካይ በታች እንዳገኙ ኦክስፋም አመልክቷል፡፡

የመሬት ስምምነቶች በተለያዩ የአፈፃፀም ደረጃዎች ለሙስና የተጋለጡ ሊሆኑ ይችላሉ.

ግሎባል ዊትነስ በነዚህ አይነት ስምምነቶች ውስጥ ሙስና ትልቅ ሚና የሚጫወትባቸውን ስድስት ደረጃዎች ያጎላል፡ 1) የመሬት አከላለል እና የባለቤትነት ዕቅዶች መውጣት; 2) የመሬት አጠቃቀም መርሃግብሮችን ዲዛይን ማድረግ እና መሬትን "ከጥቅም ውጭ" ወይም "ክፍት" መለየት; 3) የመሬት መውረስን ለማስረዳት 'የህዝብ ዓላማ' ወይም 'ታዋቂ ጎራ' ድንጋጌዎችን መጠቀም; 4) መሬትን በመንግስት ወይም በማህበረሰብ መሪዎች ለባለሀብቶች መሸጥ ወይም ማከራየት; 5) ከመሬት ጋር በተያያዙ ቅሬታዎች ውስጥ የመፍትሄዎች ልምምድ (እንደ የተመለሰ መሬት ወይም ትክክለኛ ካሳ); እና 6) በድህረ-ፕሮጀክት ጊዜ ውስጥ የባለሀብቶችን ግዴታዎች መቆጣጠር.

## የከተማ መሬት አስተዳደርና ሙስና በኢትዮጵያ

በፍጥነት እያደገ ከሚሄደው የከተማ ህዝብ አንፃር - ለምሳሌ በኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ በአለም ፈጣን እድገት እያስመዘገቡ ካሉት የከተማ አካባቢዎች አንዱ ነው (አዲስ ጂኦግራፊ 2012) - የከተማ መሬት እና በቂ መኖሪያ ቤት ማግኘት በጣም ተፈላጊ እየሆነ መጥቷል፡፡ (የዓለም ባንክ 2012). ኢትዮጵያ ውስጥ የመሬት ተደራሽነት እጅግ በጣም አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ትልቅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሀብት ሆኗል፡፡

ሙስና በኢትዮጵያ አሳሳቢ ችግር እንደሆነ ይታሰባል፡፡ በ2013 በትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የሙስና አመለካከቶች መረጃ ጠቋሚ ከ177 ሀገራት 111ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል፣(Transparency International 2013a)

እ.ኤ.አ. በ2013 የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ግሎባል ሙስና ባሮሜትር ምላሽ ሰጪዎች (43%) በኢትዮጵያ ያለው የሙስና መጠን ጨምሯል ብለው ያስባሉ፡፡

በኢትዮጵያ በመሬት አስተዳደር ሴክተሩ በአገሪቱ የፌዴራል የሥነ ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የምርመራ ቁልፍ የትኩረት መስክ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በ2007/2008 ዓ.ም ዓመታዊ ሪፖርት፣ በዓመቱ ከተመረመሩት 63 ጉዳዮች 28ቱ በመሬት አስተዳደርና ልማት ዘርፍ (የዓለም ባንክ 2012b) ናቸው፡፡

በመሬት ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና ከጥቃቅን/ቢሮክራሲያዊ ሙስና በሐራጅ ሒደቶች እስከ መንግሥት ባለስልጣናትን መማረክ ድረስ የተለያየ መልክ ሊኖረው ይችላል፡፡ የጉቦ ክፍያ እና መደበኛ ያልሆነ ክፍያ እንዲሁ በመሬት ዘርፍ ውስጥ ይከሰታል፡፡ እንደ ፌ.ስ.ፀ.ሙ.ኮ. (FEACC) ገለጻ፣ መደበኛ ያልሆኑ ክፍያዎችን ተቋማዊ ማድረግ በመሬት ዘርፍ በጣም የተለመደ እየሆነ መጥቷል፣ FEACC "የከተማ አስተዳደር ባለሥልጣናትን ያለ ጉቦ መሬት ማግኘት ፈጽሞ የማይቻል ነው" (የዓለም ባንክ 2012a)

ከዚህም በላይ ሌላው ጉዳይ የባለሥልጣናት መሬት ለራሳቸው ለመስጠት የሚያደርጉት የማጭበርበር ተግባር ነው፡፡ በእርግጥ በአዲስ አበባ ውስጥ ባለፉት አምስት ዓመታት (የዓለም ባንክ 2012) ወደ 15,000 የሚጠጉ ፎርጅድ ርዕሶች ተሰጥተዋል ተብሎ ይገመታል፡፡

አሁን ባለው የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ ብልሹ ድርጊቶች እንዲፈጸሙ የሚያስችል መግቢያ ነጥብ ሊፈጥሩ የሚችሉ በርካታ አካላት አሉ፡፡ እነዚህም ግልጽ ፖሊሲዎች አለመኖር፣ ደካማ ተቋማት፣ የግልጽነት ጉድለት እና የህዝብ ተሳትፎ ውስንነት እና የአቅም ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ .

## የግንባታ ሙስና፡

ኢንዱስትሪው ውስብስብ እና መደበኛ ያልሆኑ የምርት ሂደቶችን ስለሚያካትት፣ በደንበኞች እና በአቅራቢዎች መካከል ያልተመጣጠነ የመረጃ ክምችት መኖርና፣ ከመንግስት ጋር ካለው ብዙ ቅርበት፣ የተነሳ ግንባታ በአለም አቀፍ ደረጃ በሙስና ከተዘፈቁ ኢንዱስትሪዎች አንዱ ሆኖ መያዙ የሚያስደንቅ አይደለም፡፡

የቢዝነስ ግንዛቤዎችን ስንመለከት፣ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ባደረገው 15 የአገር ውስጥ የሕዝብ አስተያየት ግንባታን በሙስና የተዘፈቁ ኢንዱስትሪዎች አድርጎ አስቀምጧል፡፡

በአገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ኩባንያዎች የዳሰሳ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ግንባታው ከመንግስት ውል ጋር በተያያዘ ለሙስና የተጋለጠ ኢንዱስትሪ ነው ፡፡

የቢዝነስ አካባቢ እና ኢንተርፕራይዝ አፈጻጸም ዳሰሳ (BEEPS) በ22 የሽግግር አገሮች ውስጥ ከ4,000 በላይ ድርጅቶችን የሚሸፍን ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው በ1999-2000 ነው፡፡ በ1999 መካከለኛ ኩባንያ ከገቢው አንድ እስከ ሁለት በመቶ የሚሆነውን ለመደበኛ ባልሆኑ ክፍያዎች ወጪ ለህዝብ ባለስልጣናት ማድረጉን ዘግቧል፡፡

በ BEEPS ውስጥ የተወከሉት የግንባታ ድርጅቶች ከአማካይ ድርጅት የበለጠ ትልቅ 'የጉቦ በጀት' አላቸው፣ እና ብዙ ጊዜ ጉቦ ይሰጣሉ፡፡ ከጠቅላላው የጉቦ በጀታቸው ውስጥ ትልቅ መቶኛ የመንግስት ኮንትራቶችን ለማግኘት ያወጣሉ፡፡

በምስራቅ አውሮፓ የሚገኙ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች በኢንዱስትሪያቸው ውስጥ የመንግስት ውልን ለማስጠበቅ የሚደረገው የተለመደ ክፍያ ከኮንትራቱ ዋጋ ሰባት በመቶ ያህል እንደሆነ ያምናሉ፡፡ በ BEEPS ውስጥ ያሉ የግንባታ ድርጅቶች ለፈቃዶች እና ለፈቃዶች ክፍያ የመክፈል እድላቸው ሰፊ መሆኑን ሪፖርት ያደርጋሉ (ምንም እንኳን ይህ ከጉቦ በጀታቸው ያልተለመደ ትልቅ ድርሻ ባይወስድም)፡፡

ከዓለም አቀፍ የኢንተርፕራይዝ ጥናቶች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በተለያዩ አገሮች የግንባታ ፈቃድ የቁጥጥር መስክ ለሙስና የተጋለጠ ሆኖ ይታያል፡፡ በአብዛኛዎቹ አገሮች የአሰራር ሂደቱ በተለይም የሥራ ፈቃድ ከማግኘት ሂደት ወይም ከሂደቱ የበለጠ ብልሹ ነው ፡፡ የዳሰሳ ማስረጃዎች በሴክተሩ ውስጥ ያሉ የሙስና ዓይነቶችን የተለያዩ መሆናቸውን ይጠቁማሉ - የበጀት ውሳኔዎችን ፣ የፕሮጀክት ምርጫን ፣ የጨረታ ዝርዝሮችን ፣ የግዥ ውጤቶችን ወይም የኮንትራት ድርድርን እና ድጋሚ ድርድርን ለመቆጣጠር ከተነደፉ ጉቦዎች ጀምሮ ጥራት የሌላቸው የግንባታ ልምዶችን እና ውጤቶችን ለመሸፈን በተዘጋጀ ጉቦ እስከ የቁሳቁሶች ስርቆት፡፡ ማስረጃው እንደሚያመለክተው ሙስና ለግንባታ ጉድለት፣ ለደህንነት ውስንነት እና ለመንግስት መሠረተ ልማት ብክነት መሰረት ነው፡፡

References:

1. Giz (2020) trends in urban corruption and how they shape urban spaces, german federal ministry for economic cooperation and development, eschborn, germany
2. Laura nkula-wenz, liza cirolia and stephen berrisford (2023) corruption in urban planning፡ a guide for professional and trainee planners, transparency international
3. Rahman, kaunain (2022) housing policy: corruption risks and potential safeguards, transparency international
4. Kaunain rahman , (2022), housing policy: corruption risks and potential safeguards, transparency international anti-corruption helpdesk answer, tihelpdesk@transparency.org,
5. Charles kenny , (2007), construction, corruption, and developing countries, world bank policy research working paper.
6. Samira Lindner, (2014), overview of corruption in land administration inn Ethiopia, Transparency international

# ክፍል 3፡ የጥናቱ መረጃ ሂደት፣ የትንተና ዘዴና ተግዳሮት

## *3.1. የጥናቱ ቦታ*

ጥናቱ የተካሄደው የከተማ እና መሰረተ ልማት ዘርፍ በተደራጁ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እና የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ነው፡፡

## *3.2. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች*

ለጥናቱ ክንውን የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ቼክ-ሊስት (የዳሰሳ መጠይቅ) እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ሲሆኑ ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

**ቼክ-ሊስት፡-** የጥናት ቡድን አባላት የተቋማት የተለያዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በማወያየት እንዲሁም (እንዳስፈሊጊነቱ) በምልከታ የተዘጋጀውን ቼክ-ሊስት እንዲሞላ ተደርጓል፡፡ ይህን ጥናት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በቼክ-ሊስት ላይ የተነሱ ነጥቦች አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጣቸው በሰነድ ወይም በምልከታ ሲረጋገጡ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የሙስና ግንዛቤ (perception) ጥናት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ነው፡፡

**ሰነዶች፡-** የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከል ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ተዳሰዋል፡፡

**የሃሳብ ማጎልበቻ ዉይይት፡-** እንደሚታወቀው የሙስና ስጋቶች ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም የመለያየት ባሕሪ አላቸው፡፡ ስለሆነም ተቋም-ተኮር የሙስና ስጋት ልየታ ለማካሄድ በጥናቱ በተካተቱ ተቋማት ውስጥ የበርካታ አመታት ዕውቀት ካላቸው በጥንቃቄ ከተመረጡ ሃሊፊዎች እና ባለሙያዎች (experts) ጋር ሃሳብ የማጎልበት ውይይት ተካሂዷል፡፡

### *3.3. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ*

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ነው፡፡ ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) አሀዛዊ መረጃዎችን (የፕሮጀክቶች የወጪ መረጃና አፈፃፀም፣ የግዥ አፈፃፀም ማሳያዎች፣ የውጭ እና የውስጥ የኦዲት ሪፖርት ግኝቶች፣ ወዘተ) በመተንተን ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች (ቼክ-ሊስት፣ ሰነዶች እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን በመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ተጠቅሟል፡፡

### *3.4. የጥናቱ ተግዳሮቶች*

በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

በዘርፉ ያሉ አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች በተያዘላቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ፕሮግራም መሰረት ያለመገኘት፤ የተቋማት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን የተሟሉ ሰነዶችን አለማቅረብ እና የተቋማትን ማስረጃ በጥራት ለመሰብሰብ የተሠጠው ጊዜ በአመዛኙ በቂ አለመሆን፣ የ2014 በጀት ዓመት የውጭ ኦዲት ሪፖርት ተጠናቆ ለተቋማት አለመድረሱ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

# ክፍል 4፡ ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት ትንተና

የከተማ እና መሰረተ ልማት ዘርፍ የስራ አፈጻጸምና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ትንተና በ11 ርዕሰ-ጉዳዮች ተከፋፍሎ ተተንትናል፡፡ እንደሚታወቀው በሀገራችን በዚህ ዘርፍ የሚከናወኑ ተግባሮች ሀ. በሙስና የሚፈጸም የመሬት ወረራና ዝርፊያ፣ ለ. በኮነስትራክሽን ዘርፉ ባሉ የሙስና ችግሮች ጥራት የጎደላቸው፣ ረዥም ጊዜ የሚፈጁና ዋጋቸው የናረ መሆን ሐ. የማዘጋጃ አገለግሎትን በተመለከተም የሚሰጡ አገልግሎቶቸ ዜጎችን ያማረሩና ለችግር የዳረጉ እንደሆኑ በተለያዩ ሚዲያዎች በሚሰራጩ ዜናዎች፣ የየተቋማቱ ሃላፊዎች ከሚያደርጉት ገለጻዎችና ከያንዳንዱ ዜጋ የሚሰማ እሮሮ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። የዚህ ጥናት ዉጤት እንኚህ ችግሮችን ከማቃለል አንጻር የራሱ አስተዋጽኦ አለው ተብሎ ይታምናለ፡፡

## *4.1. የተቋሙ አደረጃጀት*

በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ ስር የሚገኙ ተቋማት ሁሉም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸውን በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት ያቋቋሙ ሲሆን ይህም 81.25 በመቶ የሚሆኑ የሥራ መደቦች በሰው ኃይል የተሟላ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ይሁንና 19.75% የሚሆኑት የዘርፉ የስራ መደቦች በሰው ሃይል አለመሸፈናቸውን በመረጃ ማረጋገጥ ተችሏል። ይህም የሙስና መከላከል ስራው ላይ አሉዊ ተጽእኖ አለው፡፡ በሁሉም ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አመታዊ ዕቅድ እንዳላቸውና ለስራ ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት በፑል የተመደበላቸውና አስፈላጊ የስራ ቁሳቁሶች ማሟላታቸው በተደረገው ምልከታና የሰነድ ማስረጃ ለመመልከት ተችሏል፡፡

በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ተጨማሪ የሀብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ማለትም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የግዢ ኮሚቴ፣ የደረጃ እድገት ኮሚቴ፣ መኖራቸው የተረጋገጠ ሲሆን ሁለት ተቋማት ግን (50 በመቶ) የህግ ባለሙያ

የላቸውም፡፡ የሕግ ክፍል በተቋቋመባቸው ተቋማት ውሎች ላይ ተከታታይነት ያለው ድጋፍና ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር እንዳለ ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የስራ ክፍሉ አለመኖሩ የተፈጠሩ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን በህግ አግባብ ለመዳኘት ካለማስቻሉም ባለፈ ሙሰኞች ከተገባራቸው መማር እንዳይችሉ ያደርጋል፡፡

በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል የሃሳብ መስጫ ሳጥን፣ ኢ-ሜይል፣ እና ስልክ ተደራሽ የጥቆማ መስጫ ሥርዓት መዘርጋቱን በተደረገው ምልከታና የሰነድ ማስረጃ ለማወቅ ተችላል፡፡ የሥነምግባር መከታተያ ክፍች ከሌሎች የስራ ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር ከሚደረግ የሥራ ግንኙነት ውጭ ሥራዎችን በጋራ ሊያሠራ የሚያስችል እና በሰነድ የተደራጀ መደበኛ ቅንጅታዊ አሰራ ስርዓት አለመዘርጋቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ዘርፉ የሕግ ክፍል ራሱን ችሎ በተቋቋመባቸው ተቋማት ውሎች ላይ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ እንደሚያደርግ እንዲሁም ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ስርዓት እንዳለ ከሰነዶች ማረጋገጥ ቢቻልም፤ በተወሰኑትና የሰው ሃይል ባልተሟላቸው ተቋማት በውሎች ላይ አስተያየት እየተሰጠ ሥለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ አልተቻለም፡፡ ይህም የስራ ሃላፊዎች በስህተት ከህግ ድንጋጌ ዉጭ እንዲከዉኑና አላስፈላጊ ስህተትና ሙስና ሊዳርጋቸው ይችላል፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ተቋማት የተለያዩ ክፍሎች ላይ አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት መኖሩን የሚያሳይ መረጃ ስለመኖሩ የቀረበ ሰነድ የለም፡፡

**ተቋማዊ አደራጀትን በተመለከተ ከላይ በዘርፉ በቀረበው የሰነድ ትንተና መሰረት የሚከተሉት ክፍተቶችና የሙስና ሲጋቶች ተስተውለዋል፡**

- የተወሰኑ በዘርፉ የሚገኙ የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ክትትል የስራ መደቦች በሰው ሃይል አለመሸፈናቸው በክፍሉ በቂ የሰው ሃይል እንዳይኖረው በማድረግ ስራዎች በወቅቱ እንዳይሰሩና ክፍሉ በተሟላ የሰው ሀይል ጠንካራ እንዳይሆን በማድረግ የሙስና መከላከል ስራው ላይ አሉዊ ተጽእኖ አለው፡፡

- በተወሰኑ ተቋማት ተቋማዊ የህግ ባለሙያ አለመኖር ብልሹ አሰራሮች ሲከሰቱ አጣርቶ ተጠርጣሪዎችን ለህግ የሚያቀርብ እና ተዛማጅ ህጋዊ አስተያየቶችን መስጠት የሚችል ባለሙያ የለም ማለት ነው፡፡ በዉሎችና ሌሎች ስራዎች ላይ የህግ አስተያየት አለመቀበል የተፈጠሩ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን በህግ አግባብ ለመዳኘት ካለማስቻሉም ባለፈ ሙሰኞች ህግን እንዳይፈሩና ከሙስና ተግባራቸው መማር እንዳይችሉ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የስራ ሃላፊዎች በስህተት ከህግ ድንጋጌ ዉጭ እንዲከዉኑና አላስፈላጊ ስህተትና ሙስና ዉስጥ እንዲገቡ ሊዳርግ ይችላል፡፡

- የተደራጀ መደበኛ ቅንጅታዊ አሰራ ስርዓት አለመዘርጋቱን ሌላው ስጋት ነው፡፡ ሊያሠራ የሚያስችል እና በሰነድ የተደራጀ የተቀናጀ አሰራር ስርአት አለመኖር ስራዎችን በሃላፊነታቸውና በሙያቸው ልክ በመወያየት ሊፈቱ የሚችሉትን አቅም በማሳነስ ሙሰናና የሙስና ስጋት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡

ከላይ ባለው ትንትና መሰረት በዘርፉ ያለው ተቋማዊ አደረጃጀት ጥሩ የሚባል ቢሆንም በዘረፉ በተቋማቱ የሙስና መከታተያ ክፍል የተሟላ የሰው ሃይል አለመኖር፣ ግማሽ በሚሆኑ ተቋማት የህግ የስራ ክፍል አለመመደቡና፣ አጠቃላይ  በዘርፉ ሙስናን ለመከላል የሚያስችል መደበኛ የሆነ የጋራ እቅድ ያለውና አፈጻጸሙ የሚገመገም የቅንጅታዊ አሰርር ስርኣት አለመኖር መጠነኛ የሙስና ስጋት መኖሩን ያሳያል፡፡

## *4.2. ተጠያቂነት ማስፈን*

በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ ከሚገኙ 4 ተቋማት ሶስቱ የሙስና ስጋት ጥናት ያካሄዱ መሆኑ ቢታወቅም ጥናቶቹን ተመርኩዞ የአሰራር ማሻሻያዎች እንደተደረገ በቃል ከመግለፅ ባሻገር ማስረጃ አልቀረበም፡፡

የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀትና መተግበርን በተመለከተ ሁሉም የዘርፉ ተቋማት ያዘጋጁ መሆኑን ከሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ ቢቻልም ወቅታዊ አለመሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የተሳሳቱ ድርጊቶች (ህጋዊ አሰራርን ያልተከተሉ ድርጊቶች) ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎች ተግባራዊ እንደሆኑ የሚያሳይ መረጃ የቀረበ ባይሆንም፤ በስነ ምግባር ጉድለት ምክንያት በሶስት ተቋማት ውስጥ

38 ፈጻሚ ባለሙያዎች እንዲሁም 2 አመራሮች በድምሩ 40 የሚሆኑ ክሶች ቀርበው 39 ወሳኔ ያገኙ መሆናችው ተረጋግጧል፡፡ አፈፃፀሙም 97 በመቶ ሲሆን 1 ክስ  በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በዘርፉ ስር በሚገኙ ተቋማት የህግ ክፍል ባለፉት ሁለት ዓመታት በፍትሀብሔር እና በወንጀል 108 ክሶች እንዲመሰረቱ በማድረግ በአብዛኛው 76.9 በመቶ በሚሆኑ ክሶች ላይ የተቋማቱ የህግ ክፍል ያሸነፈባቸው ሲሆኑ በቀሪዎቹ በ23.1 በመቶ ክሶች ተሸንፈዋል፡፡

በዘርፉ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓትንና የቀረቡ ቅሬታዎችን በተመለከተ ከአንድ ተቋም ከቀረበ ቅሬታ በቀር በሌሎች ተቃማት የቀረበ ቅሬታ አለመኖሩን የቀረቡ ሰነዶች ያሳያሉ፡፡  ከአንድ ተቋም የቀረበው ቅሬታም ውሳኔ ማግኘቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ አፈፃፀም ሪፓርት በየሩብ ዓመቱ በተቋማቱ የበላይ አመራሮች ክትትልና ግምገማ እንደሚደረግ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ተቋማዊ ተጠያቂነት ርእሰ-ጉዳይን በተመለከተ ከላይ በዘርፉ በቀረበው የሰነድ ማስረጃና የተሰጠ ትንተና መሰረት የሚከተሉት ክፍተቶች (የሙስና ስጋቶች) ተስተውለዋል፡**

**ተቋማዊ ተጠያቂነት በተመለከተ ከላይ በዘርፉ በቀረበው የሰነድ ትንተና መሰረት፡** በዘርፉ የሙስና ስጋት ጥናት መደረጉ ጠንካራ ጎን ቢሆንም

- ድርጅቶች የስነምግባር ደንባቸውን ወቅታዊና ከተሻሻሉ ህጎችና አሰራር ስርአቶች ጋር የተገናዘቡ መሆን አለባቸው፡፡ ወቅታዊ ያልሆነ ደንብ ወቅታዊ አሰራሮችን፣ የቴክኖሎጂና ማህበረሰብ እድገትን ባለማገናዘቡ የሰራተኛውን ዉጤታማነትና የስራ ባህሪ በሚጠበቀው ደረጃ አይቀርጸውም፡፡ ለብልሹ አሰራርና የስራ ባህሪ ይዳርገዋል፡፡
- በዘርፉ የቅሬታ መቀበያ ስርዓት እንደተዘረጋ ቢገለፅም አብዛኞቹ የዘርፉ ተቋማት የቀረበ ቅሬታ እደሌለ መገለፁ ለቅሬታ መቀበያ የተዘረጋውን ስርዓትና የቀረቡ ቅሬታዎችን የማደራጀት ስራ ንጽህናና ጥንካሬ ላይ ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ ይታያል፡፡

የከተማ እና መሰረተ ልማት ዘርፍ ተቋማዊ ግልጽነት መልካም ደረጃ ላይ ይገኛል ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ሲሆን ከላይ በክፍተት የተነሱት ስጋቶች መጠነኛ የሙስና ስጋት እንዳለ ያሳያል፡፡

## 4.3. የተቋማት ግልፅነት

በከተማ እና መሰረተ ልማት ዘርፍ ያሉ ሁሉም ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድ፣ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ከሠራተኞችና ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እንደሚደረግባቸውና የእቅድ አፈፃፀሙም የመልካም አስተዳር ችገሮች የለየ እንደሆነ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በተለያዩ የሚዲያ አማራጫቾን ተጠቅመው ተደራሽ እያደረጉ ስለመሆኑ በተደረገው ምልከታ (የሰነድ ማስረጃ) ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪ ሁሉም ተቋማት የሚሰጡ ውሳኔዎችን ተደራሽና አሳታፊ እያደፈረጉ እንደሆነ (የስብሰባ ጥሪ ደብዳቤዎች፣ ቃለ ጉባኤ፣ የሰነድ ምልከታ)ማረጋጥ ተችሏል፡፡

የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን በተመለከተ በዘርፉ ያሉ ተቋማት የአገልግሎትና የእቃ ግዢና ጨረታ ማስታወቂያዎችን በጋዜጣ፣ በቴሌቪዥን እና በድህረ ገጽ ተደራሽ የሚደረግ ሲሆን በተጨማሪም የማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም መረጃዎችን እንደሚያሰራጩ በተደረገው ምልከታ/የሰነድ ማስረጃ/ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ተቋማዊ ግልጽነትን በተመለከተ ከላይ በዘርፉ በቀረበው የሰነድ ትንተና መሰረት፡**

በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ግልጽነትን በተመለከተ በተደረገው ትንንተና የታዩ ውጤቶች አወንታዊ እንደሆኑ ቢያሳዩም ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር የበለጠ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡

## 4.4. አዋጅ ደንብና መመሪያ

በዘርፍ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ የአሰራር ስርዓትን ለማሻሻልና ለመደገፍ የሚያስችሉ 4 አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎችን በአንድ ተቋም የማዘጋጀትና የማሻሻል ስራዎች የተሰሩ ሲሆን በሌሎች ተቋማት ግን ህጎች ስለመዘጋጀታቸው በምልከታም ይሁን በሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በዘርፉ ለሚገኙ አመራሮች እና ሰራተኞች ስልጠና እንደተሰጠ ቢገለጽም የተሰጠው ስልጠና ግን የተዘረዘሩትን ህጎች መሰረት አድርጎ ሳይሆን እንደ

አጠቃላይ ከሌሎች ስልጠናዎች ጋር መሆኑንና ራሱን ችሎ የተሰራ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪ በዘርፉ ፀድቀው የሚወጡ መመሪያዎች ለተገልጋዮች/ለተጠቃሚዎች በቀላሉ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም አንድ ተቋም ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ያደረገ ሲሆን ሌሎች ግን ተደራሽ ስለማድረጋቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ እንዲሁም ሁሉም የዘርፉ ተቋማት የዜጎች ቻርተር መኖሩንና የስራ ክፍሎች ስታንዳርድ ለተገልጋዮች በየቢሯቸው በር ስለመለጠፉ መረጃዎች የሚያሳዩ ቢሆንም ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ተደራሽ ስለማድረጋቸው በተደረገው ምልከታ/የሰነድ ማስረጃ/ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ተቋማዊ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን በተመለከተ ከላይ በቀረበው ትንተና መሰረት፡ በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ አብዛኞቹ ተቋማት የአስራር ስርዓትን ቀልጣፋና ምቹ ለማድረግ የሚያስችሉ ህጎችና የአሠራር መመሪዎችን፣ የዜጎች ቻርተርን ከማሻሻልና ወቅቱን ያገናዘበ ከማድረግ አንፃር ካለው ክፍተት ውጪ በጣም ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በርእሰ-ጉዳዩ ያለው የሙስና ስጋተ ዝቅተኛ ነው፡፡

## *4.5. የተቋማት ንብረት አስተዳደር*

መረጃዎቹ እንደሚያመላክቱት የንብረት የማስተዳደርና ቁጥጥርና አሰራር ስርዓትን በተመለከተ ሁሉም ተቋማት ንብረትን መቆጣጠርና ማስተዳደር የሚያስችሉ አሰራሮችን ማለትም (ቢን ካርድ፣ ቋሚ ንብረት ምዝገባ እና IFMIS) የሚጠቀሙ መሆናቸውን እና አመታዊ የንብረት ቆጠራ እንደሚያደርጉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ነገር ግን የንብረት አያያዝና አስተዳደር አሰራር ሊያዘምን የሚያስችለውን የካይዘን ንብረት አሰተዳደር ስርዓት ከአንድ ተቋም ውጪ ተግባራዊ እንዳልተደረገ ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት አገልግሎት የማይሰጡ ወይም አገልግሎት መስጠት እየቻሉ በንብረት ክፍል (store) የሚገኙ ንብረቶች አያያዝ በተመለከተ ሊወገድ ተከማችቶ የተገኘ የንብረት ማስረጃ ባይገኝም ማስወገድን በሚመለከት በሁሉም ተቋማት የንብረት አወጋገድ ዘዴውም ህግና አሰራሩ በሚፈቅደው መሰረት ሌሎች ንብረቱን ለሚጠቀሙ ተቋማት በስጦታ እና በሽያጭ የተወገደ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- **ተቋማዊ ንብረት አስተዳደር በተመለከተ ከላይ በዘርፉ በቀረበው የሰነድ ትንተና መሰረት፡**

የዘርፉን የንብረት አስተዳደርን ስርአት በተመለከተም ዘመናዊ የንብረት አስተዳደር ስርዓት (የካይዘን ስርዓትን) ትግበራ በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ የየተቋማቱ ንብረት በሃላቀር የንብረት አስተዳደር ስርአት ተግባራዊ እንዲሆን በማስቻሉ የየተቋማቱን ንብረቶች ለብክነት፣ መጥፋትና፣ መጭበርበር መንገድ ስለሚከፍት በርአሰ-ጉዳዩ ያለውን የሙስና ስጋት መካከለኛ ነው ብሎ መዉሰድ ያስችላል፡፡

## *4.6. የግዥ አስተዳደር*

በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት የግዥ አስተዳደርን በተመለከተ የግዢ እቅድ እንደሚያዘጋጁ መረጃዎች ቢያሳዩም የግዥ እቅድ ግምገማ ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በዘርፉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የግዥ አፈፃፀም ግምገማ እንደሚያደርጉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዘርፉ የሚገኙ 2 ተቋማት የገበያ ጥናት በማድረግ ግዥ እንደሚፈፅሙ የተገኙ  መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ ስር የሚገኙ ተቋማት ዲጅታል የግዥ ሰርዓትን ከመጠቀም አንፃር የ IFMIS ስርዓትን ከመጠቀማቸው ውጪ የሚጠቀሙት ቴክኖሎጅ ሰለመኖሩ የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡

በዘርፉ ያሉ ተቋማት ግዥ የሚፈጽሙት በግዥ እቅድ መሰረት በስቶክ ያሉና የሌሉ ንብረቶችን በመለየት እንደሆነ ቢገለፅም ግዥ አፈፃፀማቸው እንደሚያሳየው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ማኔጅሜንት ኢንስቲትዩት የግዥ ሰነድ ማቅረብ ያልቻለ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስጣን ደግሞ የግዥ ስርዓትን ተከትሎ ከመፈጸም አንፃር ከዕቅድ ውጭ ብር 4,600,000፣ በፐርፎርማ ደግሞ ብር 6,144,510.88 ግዥ የፈፀመ መሆኑን ሰነዶች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ የግዥ ስርዓት እንደምረዳው ተቋሙ የግዥ እቅድን ተከትሎ እየሰራ አለመሆኑን ነው ፡፡

- **ተቋማዊ  የግዥ አስተዳርን በተመለከተ ከላይ በዘርፉ በቀረበው ትንተና መሰረት፡**

በዘርፍ የሚገኙ ጥቂት ተቋማት በግዥ እቅድ አለመመራት፣ የገበያ ጥናት ሳያካሄዱ ግዥ መፈጸም እና ሁሉም የዘርፉ ተቋምት ዘመናዊ የግዥ ስርዓት(EGP) አለመጠቀማቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ እነኚህ ክፍተቶች ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና አስፈላጊ

ለሆኑ ነገሮች እንዳይጠቀሙ ከማድረጉ ባሻገር ከዋጋ በላይ እንዲገዙ (ለሙስና እንዲጋለጡ) ያደርጋቸዋል፡፡ የመንግሥትን የግዥ ሥርዓት አለመዘርጋት ሕገወጥነትን ለመከላከል የሚፈጥረውን የተቋማት ጨረታ በኤሌክትሮኒክስ ግብይት ሥርዓት በማሳጣት በዘርፉ ሌብነትንና በግዢ ስርአቱ ውስጥ ባሉ አሰራሮች ያሉ የሙሰና ስጋቶችን ከፍተኛ ያደርገዋል፡፡

## *4.7. የሰው ሃበት አስተዳደር*

የአንድ ተቋም ስኬት ከሚወስኑ መስረታዊ ግብኣቶች ውስጥ በዋናነት ያላቸው የሰው ሀብት ነው፡፡ ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ሀብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ያደርገዋል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የሰው ሃብት አስተዳደር ተጋለጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደንል፡፡

የሰው ሀብት አስተዳደርን በተመለከተ አብዛኛዎቹ ተቋማት ተገቢ የሆኑ አደረጃጀቶችና ኮሚቴዎች(የቅጥር፣ የዝውውር፣ የዲሲፒሊን ኮሚቴ ወዘተ) መኖራቸው በሰነዶች ተረጋጧል፡፡ የሰራተኛ ቅጥር በሚኖርበት ወቅት ማስታወቂያዎች በውስጥ ማስታወቂያ(ቦርድ) እንዲሁም በጋዜጣ ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር አለ፡፡

ከሰው ሃብት አስተዳደር ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን በሚመለከትም በ2014 እና በ2013 በጀት አመት በአንድ ተቋም ከቀረበ እና በሂደት ላይ ከሚገኝ ቅሬታ በስተቀር በሌሎች ተቋማት የቀረበ ቅሬታ አለመኖሩን መረዳት ተችሏል፡፡

ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ የማጣራት ስራ በአንድ ተቋም ቅጥር ሲፈፅም የማጣራት ስራ ከመስራቱ በቀር ሌሎች የዘርፉ ተቋማት የነባር ሰራተኞቻቸውን የትምህርትና የስራ ልምድ ማስራጃ የማጣራት ስራ ያልተደረገ መሆኑ ተረጋግጣል፡፡ በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት የአመራሮች(ዳይሬክተርና ከዚያ በታች) በውድድር ላይ የተመሰረተ ምደባ የሚያደርጉ መሆናቸውን በቀረቡ ሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የሰው ሀብት አሰተዳደር መረጃ አያያዝ ስርዓት በተመለከተ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ስርአት መዘርጋቱን በሲስተም ምልከታ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ መልኩ የሥነምግባር ግንባታንና የስራ ላይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና በሁሉም ተቋት የሚሰራ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ተቋማዊ የሰው ሃብት አስተዳርን በተመለከተ ከላይ በዘርፉ በቀረበው የሰነድ ትንተና

የተገኘ ስጋት ያለበቂ ችሎታ እና የስራ ልምድ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ሊኖሩ ስለመቻላቸው ስራዎች በእውቀትና ችሎታ እንዳይመሩ በማድረግ የድርጅቶችን አሰራርና ውሳኔ አሰጣጥን ደካማ ያደርጋሉ፤ አግባብ ባለው ሙያ የሰለጠኑ ሙያተኞችን በሙያቸው ሀገራቸውን እንዳያገለግሉ ያደርጋል የስራ እድላቸውም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ ይህ ችግር ካለው ዘላቂ ተጽእኖና የስራ ቅልጥፍናን ማሳጣት ጉዳት የሙሰና ስጋት ደረጃውን መካከለኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 4.8. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

የሀብት ምዝገባ ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ተቋማዊ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይጋጩ በራሳቸው መንገድ እንዲመሩ ለማድረግ፣ አላግባብ የተፈራ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን ለማጋለጥ እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ትልቅ ፋይዳ ያለው ሥርዓት ነው፡፡ ሥርዓቱ በተባበሩት መንግስታት የፀረሙስና ስምምነት፣ በአፍሪካ ህብረት የሙስና መዋጊያ እና መከላከያ ስምምነት እንዲሁም የዓለም አቀፍና የአህጉር አቀፍ የፀረ-ሙስና ስምምነቶችን ተቀብለው በሚፈፅሙ ሀገራት እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም ሥርዓቱን ባለፉት አሥር ዓመታት ስትተገብር ቆይታለች፡፡ ሀብትና የገቢ ምንጫቸውን ማስመዝገብ ካለባቸው አካላት/ መካከል የፌደራል ተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በዚህ መሰረት የዘርፉ ተቋማት የሀብት ምዝገባ ስራን በሃብት ምዝገባ አወጅ ቁጥር 669/2000 መሰረት እየተከናወነ ስለመሆኑ በተደረገው ጥናት በዘርፉ የሚገኙ 6698 የተቋማት አመራና ሰራተኞች ሀብታቸውን ማስመዝገብና ማሳወቅ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ሀብታቸውን እንዳስመዘገቡ በመረጃ የተመላከተው 6359 አመራና ሰረታኞች ብቻ ናቸው፡፡

በዘርፉ አብዛኞቹ ሰራተኞችና ሃላፊዎች ሃብታቸውን ያስመዘገቡና ያሳወቁ ሲሆን በቁጥር አነስተኛ የማይባሉ ደግሞ አለማስመዝገባቸው ክፍተት ነው፡፡ ሀብት ያለማስመዝገብ በአግባብ ተሰርቶ ከተገኘ ሃብት ዉጭ ያለአግባብ የተሰበሰበ ሃብትን እንደይታወቅ ከመፍራት የሚመነጭ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ በመሆኑም ይህ ከፈተኛ የሙስና ስጋት ቀሪ ሰራተኞችን በመመዝገብ ሊቀረፍ ይገባል፡፡

## 4.9. የፕሮጀክቶች አስተዳደር

ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ እስከ ፍፃሜያቸው ድረስ አግባብነት ያላቸውን ሕጎችና መስፈርቶች ተከትለው እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ቴክኒካል ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ የተለየ የኦዲት መዋቅር ባለመኖሩ፤ በተለያዩ አካላት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ለጥራት መጓደልና ብክነትና የዋጋ መናር እየተጋለጡ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

ለዘርፉ ተጠሪ በሆኑ ተቋማት ባለፉት አምስት ዓመታት የተሰሩ ወይም እየተሰሩ የሚገኙ ፕሮጅክቶች የወጪ መረጃ እና የፕሮጀክት አፈፃፀም በተመለከተ የተገኘዉ መረጃ እንደሚያመለክተዉ ፡-

በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ ባሉ ተቋማት ባለፉት አምስት ዓመታት በዘርፉ ያሉ ፕሮጀክቶች የወጪ መረጃና የፕሮጀክቶች አፈፃጸምን በተመለከተ ተጀምረው በተያዘላቸው ጊዜ ያልተጠናቀቁ 4 ፕሮጀክቶች እንዳሉ መረዳት የተቻለ ሲሆን በመጀመሪያ ውላቸው መካተት ሲገባው ባለመካተቱ ምክንያት ተጨማሪ ስራ የተሰጠበት ፕሮጅክት አንድ እና ተቋራጭ የጠፋባቸው አራት(4) ፕሮጀክቶች መኖራቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

- **የዘርፉ ፕሮጀክት አስዳደርን በተመለከተ ከላይ በዘርፉ በቀረበው የሰነድ ትንተና፡-**
    - ከላይ በቀረበው ትንተና መሰረት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዘርፉ የፕሮጀክት አስተዳር ቁጥጥርና ክትትል ክፍተት ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንደማሳያ፡-
    - በዘርፉ ከተያዙት ፕሮጀክቶች መካከል የተወሰኑት በተያዘላቸው ጊዜ አለመጠናቀቃቸውን የሚሳየው አንድም ፕሮጀክቶቹ በቂ እውቀት ባለው ባለሙያ አለመታቀዳቸውንና ሌላው ደግሞ ያላግባብ ተጨማሪ ወጪ ለመጠየቅ ከተያዘላቸው ጊዜ በላይ እንዲሻገሩ ለማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡

ተቋራጭ የጠፋባቸውና ውል የተቋረጠበቸው ሲሆኑ ተቋራጩ ሲጠፉ ውል መቋረጡ እንደመልካም ቢወሰድም ተቋራጩ ሊጠፉ የሚችለው በጨረታ ሂደት ውስጥ ትክክለኛውን እና አቅም ያለው ተቋራጭ አለመጫረቱና በአጫራቹና በተጫራቹ መካከል በተደረገ አላስፈላጊ ግንኙነት ሊሆን ስለሚችል የዋጋ ልዩነት የታየባቸው ፕሮጀክቶች አንድም በሃገሪቱ ከእለት ወደእለት እየናረ በሚታየው የዋጋ መጨመር ሊሆን ሲችል ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በኮንትራት ሰጪና በኮንትራክተር መካከል በሚደረግ ያለአግባብ ስምምነት ሊሆን ይችላል፡፡

በፕሮጀችት አስተዳደር ዙሪያ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮች ከሚፈጥሩት የገንዘብ ወጪና ጉዳት አንጻር ከፍተኛ የሙስና ስጋተ ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

## 4.10. ኦዲትና ቁጥጥር

በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት የውጭ ኦዲት ሪፖርት በሂደት ላይ በመሆኑ የውጭ ኦዲት ሪፖርት መረጃዎች ማግኘት ባይቻልም በተቋማቱ የውስጥ ኦዲት ግን በየጊዜው ኦዲት እንደሚደረግ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይሁንና በዘረፉ ያልተወራረዱ፣ ያለአግባብ የተወሰዱ እና ተመላሽ የተደረጉ ሂሳቦች እንዳሉ በቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ የተቋማቱ አመራር የውስጥ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ እንደሚያካሂድና የተገኙ ግኝቶች ላይ ተመስርተው ማሻሻያዎች ስለመደረጋቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን የኦዲት ሪፖርቶቹ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- **የዘርፉ የኦዲት ቁጥጥርን በተመለከተ ከላይ በዘርፉ በቀረበው የሰነድ ትንተና፡-**
  - የኦዲት ቁጥጥርና አስተዳደር ስርዓቱ በውስጥ ኦዲት በማድረግ በሚገኙ ግኝቶችና በቀረቡ የማሻሻያ ሀሳቦች ውይይትና ግምገማ መደረጉ እንደመልካም የሚወሰድ ቢሆንም፤ የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች ተደራሽ አለመደረጉ የሚመለከታቸው አካላት ግኝቶችን ማስተካከል በሚያስችል መልኩ በትኩረት ለመከታተል የሚያስችል ባለመሆኑ የግልፅነት ስርዓቱን አመኔታን ሊያሳጣ የሚችልበት እድል አለው ፡፡

## 4.11. የሙሰና ስጋት

የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ማለት ታሳቢ ስጋት ሲሆን ቢከሰት የተቋሙን የአሰረር ስርዓት አደጋ ላይ የሚጥል እና ማህበረሰቡ በተቋሙ ላይ ያለውን አመኔታ የሚሣጣ ሲሆን በተደጋጋሚ በሚከሰት ብልሹ አሰራር ድግግሞሽና እና ብልሹ አሰራሩ ቢከሰት ሊፈጥር በሚችለው ተፅዕኖ ምክንያት የሚለካ ስጋት ነው፡፡ በመሆኑም ዘርፉ ባለው የስራ ባህሪ፣ ከሚያንቀሳቅሰው ሃብትና ከሚከተለው የአስራር ስርዓት አንፃር በተቋሙ ውስጥ ስለተቋሙ በቂ መረጃና ልምድ ያላቸው የተመረጡ የዘርፍ አመራሮችና ባለሙያዎች በሰጡት መረጃ መሰረት የዘርፉ የሙስና ስጋት ይሆናሉ ያሏቸውን አሰራሮች እንደሚከተው ሰጥተዋል፡፡ በዚህም መሰረት የግዥ ስርዓት፣ የንብረት/የህንፃ ጥገና፣ የምህንድስና ግዥ፣ የመንገድ ወሰን ማስከበር

ከፍተኛ የሙስና ስጋት ሆነው ሲገለፁ የነዳጅ አጠቃቀምና ምደባና ቅጥር በመካከለኛ የሙስና ስጋት ደረጃ የተቀመጡ ናቸው፡፡

- **የዘርፉ የሙስና ስጋት በተመለከተ ከላይ በዘርፉ በቀረበው የሰነድ ትንተና፡-**

- የሙስና ስጋት ጥናት በከፍተኛ የስጋት ደረጃ የተለዩትን ልዩ ትኩረት በመስጠትና ከከፍተኛ ስጋትነት በማስወጣት በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት የማህበረሰቡን አመኔታ ለማሳደግ የአገልግሎት አሰጣጡን ማሻሻል እንደሚገባ አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡

## ክፍል 5፡ የመፍትሔ ሃሳቦች (ምክረ-ሃሳብ)

በጥናት ሪፖርቱ እንደተመለከተው በከተማና መሰረተ-ልማት ዘረፍ በአስራ ሀንዱ ርእሰ-ጉዳዮች ያሉ ስርአቶችንና አሰራሮችን በመመልከት በአዎንታዊነት የታዩና በክፍተትነት የሙስና ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡ በዚህ ክፍል በክፍተትነት ለታዩ የሙስና ስጋት ለሚሆኑ ጉዳች መፍትሄ ሊሆን ይችላል ተብለው የሚታመኑ ምክረ-ሃሳቦች ተቀምጠዋል፡፡ በዘርፉ ያሉ ተቋማት የተሰጡትን የመፍትሄ ሃሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ቢችሉ ይታዩ የሙስና ስጋቶችን በመቅረፍ የተሰጣቸውን ሀገራዊ ሃላፊነት በመወጣት ያስችላቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- የህግ የስራ ክፍል መልካም አስተዳደርን ከማስፈን፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል እንዲሁም ግልፅነት እና ተጠያቂነት ከመስፈን አንፃር ድርሻው የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም በከፊል በዘርፉ ያሉ ተቋማት በበቂ ሁኔታ ያላደራጁትን ይህንን ክፍል አግባብ ባለው መልኩ በማደራጀት ህገወጥነትን በመዋጋት ተጠያቂነተ እንዲሰፍን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ የስራ ክፍሎችን ወጥና መደበኛ በእቅድ ላይ በመመስረት በየጊዜው መገምገም የሚያስችል ስርዓት ቢዘረጋ ለሙስና ትግሉ አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው፡፡፤ በመሆኑም በጋራ የሚሰሩበት መንገድ ቢመመቻች፡፡
- በዘርፉ በተዘረጉ የጥቆማ መስጫ እንዲጠቀሙና የሙስና ስጋቶች ከመከሰታቸው በፊት መረጃ መስጠት የዜግነት ገዴታ መሆኑንና አገራዊ ጠቀሜታውን ለየድርጅቱ ሰራተኞችና አመራሮች ተከታታይነት ያለው ስልጠና መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- የንብረት አስተዳደርን ስርአት በተመለከተ ዘመናዊ የንብረት አስተዳደር ስርዓት (የካይዘን ስርዓትን) ትግበራ በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ይህ አሰራር የንብረት ብክነትን በመቀነስ፣ ደህንነትን በማሳደግ የስራና የሰራተኞችን ቅልጥፍና

በመጨመር አላስፈላጊ ወጪዎችን ይቀንሳል፣ ለብልሹ አሰራር የሚዳርጉ አሰራሮችን ይቀንሳል፡፡

- የዘርፉ ተቋምት ዘመናዊ የመንግስት የግዥ ስርዓት(EGP) በመጠቀም ሕገወጥነትን በመከላከል ከዚህ ዘመናዊ የግዥ ስርአት የሚገኘውን ዘርፈ-ብዙ ጥቅም አግኝተው በግዢ ስርአቱ የሚከስተውን የሙስና ስጋት ሊቀንሱ ይገባል፡፡
- ሙስና እና ብልሹ አሰራር ቅርፀ ተለዋዋጭና ውስስብ ስለሆነ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጣቻውን ግልፅና ቀልጣፋ ለማድረግ የሚያስችሉ የዜጎች ቻርተርን ጨምሮ ሌሎች የአልግሎት አሰጣጥ መመሪያዎችንና ደንቦችን ከወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ወቅታዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የፕሮጀክት አስተዳደር ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ክፍተት የሚታይበት በመሆኑ በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት የፕሮጀክቶች የቁጥጥርና ክትትል ስርዓታቸውን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ሙያዊ ፍተሻና ማስተካከያ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በዘርፉ የመረጃ አያያዝ ክፍተት እንዳለ በመስተዋሉ በዘርፉ ያሉ ተቋማት የመረጃ አያያዝ ስርዓታቸውን ማሻሻልና በዘመናዊ አሰራር መቀየር የሚያስችል ስርዓት ቢዘረጋ፤
- የተጀመረው የሰራተኞችና ያመራሮች የሃበት ማሳወቅና ምዝገባ ስርአት ለሁሉም ሰራተኞችና አመራሮች ተደራሽ ቢሆን፤
- በአጠቃላይ በዘርፉ በእያንዳንዱ መጠይቅ ላይ እንደተጉድለት የታዩ ሃሳቦችን እንደግብዓት በመውሰድና ሙስና እና ብልሹ አሰራር በመከላከል የዘርፉ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጡን ማሻሻል እንደሚገባ ያመላክታል፡፡